የኢትዮጵያዊው ጃንደረባ
ትውልድ

# የመሐረነ አብ ጸሎት

በግዕዝ እና በአማርኛ

# መሪ እና ተመሪ (በመቀባበል)

## ሃሌ ሉያ፤

ዘበእንቲአሃለ ቤተ ክርስቲያን

ተጸፋዕከ በውስተ ዓውድ፤

ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ሃሌ ሉያ፤

# ሃሌ ሉያ፤

(ቅድመ ዓለም የነበረ፥አሁንም ያለ፥ድኅረዓለም የሚኖር)፤

## + ዘበእንቲአሃ ለቤተ ክርስቲያን

ለቤተ ክርስቲያን ስትል

# ተጸፋዕከ በውስተ ዓውድ

በአደባባይ በጥፊ የተመታህ

# ከመ ትቀድሳ በደምከ ክቡር

አቤቱ ይህን ማድረግህ እርሷን በከበረ ደምህ ትቀድሳትዘንድ ነው፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ዘበእንቲአሃ ዝግኀታተ መዋቅሕት ፆረ

# ወተዐገሠ ምራቀ ርኩሰ እንዘአልቦ ዘአበሰ

# አምላክ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ

ለእርሷ ሲል ታስሮ መጎተትን የቻለ፤

የበደለው    በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅን ሲተፋበትየታገሰ

አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ

# ሃሌ ሃሌ ሉያ አርእየነ እግዚኦ ሣህለከ

# ረዳኤ ኩነነ ወኢትግድፈነ

# መሐረነ መሐከነ እግዚኦ እግዚኦ ተሣሃለነ

ሃሌ ሃሌ ሉያ አቤቱ ይቅርታህን አሳየን፤

ረዳት ሁነን አትተወን ፤ ማረንራራልን

አቤቱ ይቅርም በለን፡፡

# በቀኝ እና በግራ (በመቀባበል)

## መሐረነ አብ

አብ ሆይ! ማረን

## ሃሌ

## ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# ተሣሃለነ ወልድ፥

ወልድ ሆይ! ማረን

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# መንፈስ ቅዱስ መሐሪ
# ተዘከረነ በሣህልከ፤

መሐሪ መንፈስ ቅዱስሆይ!
በይቅርታህ አስበን፡፡

# መሐረነ አብ

አብ ሆይ! ማረን

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# ተሣሃለነ ወልድ፥

ወልድ ሆይ! ማረን

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# መንፈስ ቅዱስ መሐሪ
# ተዘከረነ በሣህልከ፤

መሐሪ መንፈስ ቅዱስ ሆይ!
በይቅርታህ አስበን፡፡

# መሐረነ አብ

አብ ሆይ! ማረን

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# ተሣሃለነ ወልድ፥

ወልድ ሆይ! ማረን

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤

# መንፈስ ቅዱስ መሐሪ
# ተዘከረነ በሣህልከ፤

መሐሪ መንፈስ ቅዱስ ሆይ!
በይቅርታህ አስበን፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ለከ ንፌኑ ስብሐተ
# ወለከ ነዓርግ አኰቴተ፤

ለአንተ ምስጋናን እንልካለን፥ለአንተም ምስጋናን እናሳርጋለን፤

# መሐረነ መሐሪ ኃጢአተነ አስተሥሪ፤

ይቅር ባይ ሆይ ይቅር በለን፥ኃጢአታችንንምአስተስርይልን፤

# ወአድኅነነ፤

አድነንም፤

# ወተማኅጸን ነፍሰነ ወሥጋነ፤

ነፍሳችንንና ሥጋችንን ጠብቅ፤

# ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ሆይ!

# አምላክነ፥

አምላካችን

# ወመድኃኒነ

መድኃኒታችን

## ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ፤

ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ይቅርበለን፤

# በብዝኃ ምሕረትከ፤

በምሕረትህ ብዛት፤

# ደምስስ አበሳነ፤

በደላችንን አጥፋልን፤

# ወፈኑ ሣህለከ ላዕሌነ፤

ይቅርታህንም ወደኛ ላክልን፤

# እስመ እምኀቤከ፤

ከአንተ ዘንድ ነውና፤

# ውእቱ ሣህል፤

ይቅርታ፤

# ሃሌ ሉያ፥ መሐረነ አብ መሐሪ፤

ሃሌ ሉያ፥ ይቅር ባይ አባት ሆይ ማረን፤

# ወተሣሃለነ፤

ይቅርም በለን፤

# ሀብ ሣህለከ መሐሪ፤

ይቅር ባይ ሆይ! ይቅርታህን ላክ፤

# ኢታጥፍአነ ተዘኪረከ ዘትካት፤

ያለፈው በደላችንን አስበህ አታጥፋን፤

# በምሕረትከ፤

በይቅርታህ፤

## እስመ መሐሪ አንተ፤

አንተ ይቅር ባይ ነህና፤

## ወብዙኅ ሣህልከ ለኵሎሙ እለ ይጼውዑከ፤

ለሚጠሩህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙነው፤

# ይጼውዑከ በጽድቅ፤

በእውነት ለሚጠሩህ፤

# ሰማዒ ወትረ፤

ሁልጊዜ ሰሚ ነህ፤

# ከሃሊ ዘውስተ ኢድኅኖ፤

በማዳን ጊዜ ቻይነህ፤

# ከሃሊ፤

ቻይ፤

# ዘውስተ አድኅኖ፤

በማዳን ጊዜ፤

# ለአምላክነ እስመ ጽድቅ ቃሉ፤

የአምላካችን ቃሉ እውነት ነው፡፡

# ንስአሎ ለአብ፤

አብን እንለምነው፤

# ይፈኑ ለነ ሣህሎ፤

ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ

# እስመአብ የአክል ለዘሰአሎ፤

አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና፤

# ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፤(ቅድመ ዓለም የነበረ፥ አሁንም
ያለ፥ ድኅረ ዓለም የሚኖር)፤

# ስብሐት ሎቱ ይደሉ፤

ለርሱ ምስጋና ይገባል፤

# ሃሌ ሉያ፥

# አኰቴት ሎቱ ይደሉ፤

ሃሌ ሉያ፥ለርሱ ምስጋና ይገባል፤

# ሃሌ ሉያ ፤

ሃሌ ሉያ፤

# ለክርስቶስ ለእግዚአ ኵሉ፤

ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ፤

# ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ፥ ሃሌ ሉያ፤

ሃሌ ሉያ፥ ሃሌ፥ ሃሌ ሉያ፤

# ወይእዜኒ፤

አሁንስ(እንግዲህስ)

# መኑ ተስፋየ?

ተስፋ የማን ነው?

## አኮኑ

አይደለምን፤

# እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር

# ውስተ እዴከ እግዚኦ

# አመኀጽን ነፍስየ፤

አቤቱ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ፤

# ኀበ አምላከ ምሕረት፤

ወደ ምሕረት አምላክ

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# ኀበ ንጉሠ ስብሐት፤

ወደ ምስጋና ንጉሥ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# በእግዚእየ ወአምላኪየ፤

በጌታየና በአምላኬ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አስጠብቃለሁ፤

# እምኵሉ ምግባረ እኩይ
# አድኅና ለነፍስየ፤

ነፍሴን ከክፉ ሥራ ሁሉ አድናት፤

# ኀበ አምላከ ምሕረት፤

ወደ ምሕረት አምላክ

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# ኀበ ንጉሠ ስብሐት፤

ወደ ምስጋና ንጉሥ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# በእግዚእየ ወአምላኪየ፤

በጌታየና በአምላኬ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አስጠብቃለሁ፤

# እምኵሉ ምግባረ እኩይ
# አድኅና ለነፍስየ፤

ነፍሴን ከክፉ ሥራ ሁሉ አድናት፤

# ኀበ አምላከ ምሕረት፤

ወደ ምሕረት አምላክ

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# ኀበ ንጉሠ ስብሐት፤

ወደ ምስጋና ንጉሥ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አደራ እሰጣለሁ፤

# በእግዚእየ ወአምላኪየ፤

በጌታየና በአምላኬ፤

# አመኀጽን ነፍስየ፤

ነፍሴን አስጠብቃለሁ፤

# እምኵሉ ምግባረ እኩይ

# አድኅና ለነፍስየ፤

ነፍሴን ከክፉ ሥራ ሁሉ አድናት፤

# ሀቡ፤

ኍ

## ንስአሎ፤

እንለምነው፤

## ንስአሎ፤

እንለምነው፤

# ናስተምህሮ፤

ራራልን እንበለው(እንማልደው)፤

# ለአምላክነ ጻድቅ

# እስመ ጽድቅ ቃሉ።

እውነተኛ የሆነው አምላካችን ቃሉ እውነት ነውና፤

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ፤

ሁሉን የሚችል የሚሳነው ነገር የሌለ፤

# አምላከ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን፤

የድሆች አምላክ የችግረኞች ረዳት ሆይ

# ንሕነ ኀቤከ ተማኀጸነ።

እኛ ባንተ ተማጽነናል፤

# ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ፤

ሁሉን የሚችል የሚሳነው ነገር የሌለ፤

# አምላከ ነዳያን ናዛዜ ኅዙናን፤

የድሆች አምላክ በኃዘን ላሉ አጽናኛቸው ሆይ

# ንሕነ ኀቤከ ተማኅጸነ።

እኛ ባንተ ተማጽነናል፤

# ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ፤

ሁሉን የሚችል የሚሳነው ነገር የሌለ፤

# አምላከ ነዳያን ወተስፋ ቅቡፃን፤

የድሆች አምላክ ተስፋ ለቆጠሩ ተስፋቸው ሆይ

# ንሕነ ኀቤከ ተማኀጸነ።

እኛ ባንተ ተማጽነናል፤

ኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ መሐረነ፤

ኦ ወልድ ዋህድ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ፤ ኦ

ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ ሥረይ ለነ

ሀሉ ምስሌነ

አቤቱ የሁሉ ገዢ የሆንከ እግዚአብሔር ሆይ ማረን፤ አቤቱ

አንዱ ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ተለመነን፤ አቤቱ

ጰራቅሊጦስ የጽድቅ መንፈስ ሆይ

ኃጢአታችንን ይቅር በለን ከእኛ ገርም ሁን

# እስመ አልብነ ረዳኢ በጊዜ ምንዳቤ ወኃዘን እስመ ዘእንበሌከ ባዕድ አልቦ ዘነአምር

በችግር እና በሐዘን ጊዜ ያለአንተ ረዳት የለንምና ፤
ያለአንተም ሌላ የምናውቀው የለም።

# አይቴ ውእቱ አምላኮሙ ከመ ኢይበሉነ አህዛብ
# ምህላነ ስማዕ ቃለ አብ

አህዛብ አምላካቸው ወዴት ነው
እናዳይሉን አቤቱ ምህላችንን ስማ

አይቴ ይእቲ ትምክህቶሙ ከመ ኢይበሉነ ውሉደ

መርገም ምህላነ ስምዒ ማርያም

የመርገም ልጆች መመኪያቸው ወዴት አለች እንዳይሉን

ማርያም ሆይ ምህላችንን ስሚ

# በእንተ ማርያም ወላዲትከ ምህላነ ስማዕ በእዝንከ

ስለ ወለደችህ እናትህ ማርያም ብለህ አቤቱ ምህላችንን ስማ

# በእንተ ማርያም ሐፃኒትከ ምህላነ ስማዕ በእዝንከ

ስለ አሳደገችህ ማርያም ብለህ አቤቱ
ምህላችንን ስማ

# በእንተ ማርያም ጸዋሪትከ ምህላነ ስማዕ በእዝንከ

ስለ ተሸከመችህ እናትህ ማርያም ብለህ አቤቱ
ምህላችንን ስማ

# ኤሎሄ ኤሎሄ ዘአመ ትቤ በጽራሕከ
# ተማኅፀነ ምህላነ ስማዕ አምላክነ

አምላካችን ሆይ ኤሎሄ ኤሎሄ ብለህ
አሰምተህ በተናገርከው ቃል
ለምነንሃልና አቤቱ ምህላችንን ስማ፤

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ወበከመ ዐቀብከነ

# እምነግህ እስከ ሠርክ

# ዕቀበነ እግዚኦ እምሠርክ እስከ ነግህ፤

(3 ጊዜ በቅብብል)

ከጧት ጀምሮ እስከ ማታ እንደጠበቅከን
ከማታ እስከ ጠዋትጠብቀን፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

**ተሣሃልከ እግዚኦ ምድረከ፥ ሃሌ ሉያ፥**

**ስማዕ ጸሎተነ ወስእለተነ፥ ወስረይ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ስማዕ**

**ጸሎተነ ወስእለተነ፥ ዘሰማዕኮ ጸሎቶ ወስእለቶ ለዕዝራ፥**

**ተወከፍ ምህላነ፥ ሰላመከ ሀበነ ወእማዕከሌነ ኢትርሐቅ።**

አቤቱ ርስትህን ይቅር በል፥ ሃሌ ሉያ፥ ጸሎታችንን እና አስተብቍኦታችንን ስማ፥

ኃጢአታችንንም ሁሉ አስተስርይልን፥ የዕዝራን ጸሎትና ልመና የሰማህ ሆይ! ምህላችንን

ተቀበል፥ ሰላምህን ስጠን፥ ከመካከላችንም አትራቅ።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ወሚጥ መዓተከ እምኔነ፥ ሃሌ ሉያ፥ ንዒ ጎቤየ እንቲአየ፥ ሠናይት ርግብየ፥ መዓዛ አፉሃ ከመ ኮል ወኵሉ ነገራ በሰላም።

አቤቱ ከእኛ መዓትህን መልስ፥ ሃሌሉያ፥
ያማረች ርግቤ የአፏ እስትንፋስ እንደ እንኮይ ያማረ ነው፥
ንግግሯም ሁሉ ሰላማዊ ነው፥ ርግቤ ሆይ! ወደእኔ ነይ።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# አርእየነ እግዚኦ ሣህለከ ሃሌ ሉያ

# መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ሚካኤል፥ ሰአል

# ወጸሊ በእንቲአነ፥ አዕርግ ጸሎተነ ቅድመ

# መንበሩ ለንጉሥ ዐቢይ።

የሰላማችን መልአክ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ሆይ! ስለ እኛ

ለምን፥ ጸልይም፥ ጸሎታችንንም

ከታላቁ ንጉሥ መንበር ፊት አሳርግልን፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ገብርኤል አብሠራ ለማርያም፥

# ወይቤላ ትወልዲ ወልደ፥

# ዘይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ

# ለዓለም ወአልቦ ማኅለቅት ለስላሙ።

ቅዱስ ገብርኤል ድንግል ማርያምን አበሠራት፥ እንዲህም አላት፥

ልጅን ትወልጃለሽ፥ ለዘለዓለሙ ለያዕቆብ ቤት ይነግሣል፥

ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም።

# ዮሐንስ ክቡር
# ነቢየ ልዑል ብእሴ ሰላም
# ዘንብረቱ ገዳም

የተከበረ የልዑል ነቢይ የሰላም ሰው
ዮሐንስ መኖርያው በረሃነው።።

ሰአል ለነ ጊዮርጊስ ኀበ እግዚአብሔር ወጸሊ በእንቲአነ፥
ሐረድዎ ወገመድዎ ወዘረዉ ሥጋሁ ከመ ሐመድ፥
ወወሰድዎ ኀበ ሰብአ ነገሥት፥ ረገፀ ምድረ
አንሥአ ሙታነ አባ ጊዮርጊስ ፥
በሰላም ዐደወ መንግሥተ ክብር ወረሰ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ! ወደ እግዚአብሔር ለምንልን፥ ስለ እኛም ጸልይ፡፡
አረዱት፥ ቆራረጡትም፥ ሥጋውን ፈጭተው እንደ ትቢያ በተኑት፡፡
ወደ ሰባ ነገሥታትም ወሰዱት፥ ምድርን ተረገጠ፥ ሙታንን አስነሣ፡፡
አባታችን ጊዮርጊስ በሰላም ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ፥
ርስት መንግሥተ ሰማያትንም ወረሰ፡፡

ጥምቀተ አምጽአ ሕፅወ ንግሥት ለእሊአሁ፤
እምኀበ ፊልጶስ ድኅረ ተጠምቀ ለሊሁ፤
ሰላማ አቡነ አምጽአ ለነ በዕድሜሁ፤
ለመድኃኒነ ምሥጢረ ደሙ ወሥጋሁ።

የንግሥቲቱ ጃንደረባ ለወገኖቹ ጥምቀትን አመጣ፤
በፊልጶስ እጅ እርሱ ራሱ ከተጠመቀበኋላ፤ ሰላማ አባታችንም በዘመኑ
የመድኃኒታችንን የሥጋውንና የደሙን ምሥጢር አመጣልን።

# ብፁዕ አባ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
# ዘዔለ ገዳማተ እምኀበ እግዚኡ፥ ይንሣእ ዕሴተ፥ ቦአ ገዳመ ደብረ ሊባኖስ በፍሥሐ ወበሰላም።

ብፁዕ አባታችን አቡነ ተክለሃይማኖት ከጌታው
ዋጋን ያገኝ ዘንድ ወደ ገዳማት ገሰገሰ፤ በደስታና በሰላም
ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳምገባ፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ጻድቅሰ ከመ በቀልት ይፈሪ ወይበዝኅ ከመ ዘግባ ዘሊባኖስ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ኖመ ኖመ ኢየሩሳሌም በፍሥሐ ወበሰላም።

ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል እንደ ሊባኖስ ዘግባምያድጋል፥ ገብረ መንፈስ ቅዱስ በተድላ እና በሰላም በኢየሩሳሌም ዐረፈ(አንቀላፋ)፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ሣህል ወርትዕ ተራከባ ጽድቅ ወሰላም ተሳዐማ አመ ተሰምዓ ዜናከ በዓለም ዜና ማርቆስ ክቡር መምህረ ሰላም ዘህላዌከ ገዳም።

መኖርያህ በበረሃ የሆነ የሰላም መምህር ዜና ማርቆስሆይ ዜናህ በዓለም በተሰማ ጊዜ በጎ ስጦታ እና ቅንነት ተገናኙ፤ ጽድቅ እና ሰላም ሰላም ሰላምተባባሉ፡፡

# ባርከነ አባ ንንሣእ በረከተከ፥
# በእንተ ሰላማ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን፥
# ሳሙኤል አባ ባርከነ ንንሣእ በረከተከ።

አባ ሳሙኤል ሆይ!
በረከትህን እንቀበል ዘንድ ባርከን፥
ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ስትል ባርከን፤
በረከትህንም እንቀበል ዘንድ።

## ማኅደረ ሰላምነ ቅድስት ደብተራ፥ እሞሙ ለሰማዕት፥ ወእኅቶሙ ለመላእክት፥ ንዑ ንስግድ ኵልነ ኀበ ማርያም እምነ።

የሰላማችን ማደሪያ የተቀደሰሽ ድንኳን፥
የሰማዕታት እናታቸው፥ የመላእክት እኅታቸው፥
ኑ! ሁላችንም ለእናታችን ለድንግል ማርያም እንስገድ።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተ ክርስቲያን ወሀቤ ሰላም መድኃኔዓለም መስቀል ለእለ ነአምን መድኃኒን።

መስቀልለዓለም ሁሉ ብርሃን ነው፡፡
የቤተክርስቲያን መሠረትም እርሱ ነው፡፡
ሰላምን የሚሰጥ መድኃኔዓለም ነው፤
ለምናምን ለእኛ መስቀል መድኃኒት ነው፡፡

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ለዓለም ወለዓለመ ዓለም፥ ሃሌ ሉያ፤

# ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ ወሰላመ

# መንፈስ ቅዱስ

# የሃሉ ማዕከሌክሙ አኃው።

የአብ ሰላም የወልድ ሰላም የመንፈስ ቅዱስሰላም

ለዘለዓለም በመካከላችሁ ይኑር፡፡

# ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ

# ወሰላመ መንፈስ ቅዱስ

# የሃሉ ማዕከሌክሙ አኃው፡፡

የአብ ሰላም የወልድ ሰላም የመንፈስ ቅዱስሰላም

በመካከላችሁ ይኑር፡፡

# ሰላመ አብ ወሰላመ ወልድ
# ወሰላመ መንፈስ ቅዱስ
# የሃሉ ማዕከሌክሙ አኃው፡፡

የአብ ሰላም የወልድ ሰላም የመንፈስ ቅዱስሰላም
በመካከላችሁ ይኑር፡፡

ይ.ካ. ሰላመ አብ ወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ወፍቅራ
ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ
ሞገሰ መስቀሉ ወሀብተ ረድኤቱ
የሃሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም።

# እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ

አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን!

(በመሪ 3 ጊዜ)

(በተመሪ 3 ጊዜ)

በቅብብል





# እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ

አቤቱ ክርስቶስ ሆይ ማረን!

(በመሪ 3 ጊዜ)
(በተመሪ 3 ጊዜ)
በቅብብል

# በእንተ ማርያም
# መሐረነ ክርስቶስ

ስለ ማርያም ብለህ ክርስቶስ ሆይ ማረን!

(በመሪ 3 ጊዜ)

(በተመሪ 3 ጊዜ)

በቅብብል





# በእንተ ማርያም
# መሐረነ ክርስቶስ

ስለ ማርያም ብለህ ክርስቶስ ሆይ ማረን!

(በመሪ 2 ጊዜ)

(በተመሪ 2 ጊዜ)

በቅብብል

# በእንተ ማርያም
# መሐረነ ክርስቶስ

## ስለ ማርያም ብለህ ክርስቶስ ሆይ ማረን!

(በመሪ እና በተመሪ 1 ጊዜ)

በኅብረት



ሰአሊ ለነ ማርያም  ምሕረተ
ወልድኪ የሐውጻነ
እምአርያም፤

ማርያም ሆይ የልጅሽ ምሕረት
ከአርያም ይጎበኘን ዘንድ ለምኚልን።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ሰአሊ ለነ ማርያም ለለሰዓቱ

# ተግባረ እደዊሁ ለወልድኪ ኢንጥፋእ በከንቱ። ኮሎ

# መዓልተ ወኮሎ ሌሊተ ብዙኃ ኃጢአተ

# ዘገበርነ በእንተ ማርያም እምከ መሐሪ መሐረነ።

ማርያም ሆይ የልጅሽ የእጆቹ ሥራዎች በከንቱ እንዳንጠፋ በየሰዓቱ ለምኚልን።ይቅር ባይ ሆይ በቀንም በሌሊትም ብዙ ኃጢአት ሠርተናልና ስለ እናትህ ድንግል ማርያም ይቅር በለን፡፡

ሥመር እግዚአ ከመ ታድኅነነ።

ኢታርምም እግዚአ ወኢትጸመመነ።

ተዘከር እግዚአ ከመ መሬት ንሕነ።

አቤቱ ታድነን ዘንድ ውደድ፤

አቤቱዝም አትበል ፤ አትናቀንም፤

አቤቱመሬት መኾናችንን አስብ።

- እግዚኦ ዕቀባ ለሀገሪትነ ኢትዮጵያ
- እግዚኦ ዕቀባ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን
- እግዚኦ ዕቀበነ ለኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን
- እግዚኦ ዕቀቦ ለፓትርያርክነ አባ ማትያስ
- እግዚኦ ዕቀቦ ለሊቀ ጳጳስነ አባ ሄኖክ

. እግዚኦ ዕቀቦ ለመምህርነ --------

- እግዚኦ ዕቀባ ለደብርነ ደብረ -------
- እግዚኦ ዕቀባ ለማህበርነ ማህበረ ባኮስ
- እግዚኦ አዕርፍ ነፍሳተ አግብርቲከ ወአእማቲከ ኵሎሙ ክርስቶሳውያን።

# ስብሐት ለእግዚአብሔር
# ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ።

እናመልከው ዘንድ እኛን ለፈጠረ
ለእግዚአብሔር ምስጋን ይኹን።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ።

እመቤታችንና መድኃኒታችን ለኾነች ለአምላክ እናት ማርያም ምስጋን ይኹን።

# ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕጸ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ።

ኃይላችንና መጠጊያችን ዕጸ መድኃኒት ለሚባል ለክርስቶስ መስቀል ምስጋን ይኹን።

# ጸሎተ ሃይማኖት

ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ

አኃዜ ኲሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር

ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ፤

ወነአምን በአሐዱ እግዚእ ኢየሱስ

ክርስቶስ ወልደ አብ ዋሕድ ዘህልው

ምስሌሁ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም።

ብርሃን ዘእምብርሃን አምላክ

ዘእምአምላክ ዘበአማን።

ዘተወልደ ወአኮ ዘተገብረ ዘዕሩይ ምስለ አብ

በመለኮቱ።

ዘቦቱ ኵሉ ኮነ ወዘእንበሌሁሰ አልቦ ዘኮነ

ወኢምንትኒ ዘበሰማይኒ ወዘበምድርኒ፤

ዘበእንቲአነ ለሰብእ ወበእንተ መድኃኒትነ። ወረደ
እምሰማያት
ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ
ወእማርያም እምቅድስት ድንግል።
ኮነ ብእሴ ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ
ጰንጤናዊ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ
እሙታን አመ ሣልስት ዕለት በከመ
ጽሑፍ ውስተ ቅዱሳት መጻሕፍት፤

ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ
በየማነ አቡሁ።
ዳግመ ይመጽእ በስብሐት ይኰንን ሕያዋነ
ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።
ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማሕየዊ ዘሠረፀ
እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ
ወወልድ ዘነበበ በነቢያት፤

ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ
ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ
ዘሐዋርያት፡፡ ወነአምን በአሐቲ
ጥምቀት ለሥርየት ኃጢአት።
ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ወሕይወተ
ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም።

ይ.ካ ፡- አቡነ ዘበሰማያት ይዘዝ

# ኪዳን ዘሠርክ

# ይ.ካ. ቅዱስ

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ይ.ሕ.   እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እማርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደ ይቅር በለን።

የመሐረነ አብ ጸሎት

# ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው የማይሞት በዮርዳኖስ የተጠመቀ በመስቀል ላይ የተሰቀለ ይቅር በለን።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው
ዘኢይመውት ዘተንሥአ እሙታን አመ ሣልስት
ዕለት ዐርገ በስብሐት ውስተ ሰማያት
ወነበረ በየማነ አቡሁ ዳግመ ይመጽእ በስብሐት
ይኰንን ሕያዋነ ወሙታነ ተሣሃለነ እግዚኦ ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሕያው ቅዱስ ኃያል የማይሞት በሦስተኛው ቀን ከሙታን
ተለይቶ የተነሣ በምስጋና ወደ ሰማይ ወጣ፣ በአባቱም ቀኝ
ተቀመጠ፣ ዳግመኛም በጌትነት ይመጣል በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ አቤቱ
ይቅር በለን።

## የመሐረነ አብ ጸሎት

# ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ወአሜን ለይኩን ለይኩን።

ለአብ ምስጋና ይሁን ለወልድ ምስጋና ይሁን፣ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን፣
ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን፣ ይሁን ይሁን።

# ቅዱስ ሥሉስ እግዚአብሔር ሕያው ተሣሃለነ።

ልዩ ሦስት የምትሆን ሕያው እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን።

## ይ.ካ. ጸጋሁ ለእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ

የእግዚአብሔር ጸጋ ከእናንተ ጋር ይኹን።

## ይ.ሕ. ምስለ መንፈስከ ።

ከመንፈስህ ጋር።

## ይ.ካ. አእኵትዎ ለአምላክነ።

አምላካችንን አመሥግኑት።

## ይ.ሕ. ርቱዕ ይደሉ ።

በእውነት ይገባል።

# ንሴብሐከ እግዚኦ።

አቤቱ እናመሠግንሃለን።

# ንዌድሰከ እግዚኦ።

አቤቱ እናወድስሃለን።

## ይ.ሕ. አሜን።

## ይ.ካ ፦ አቡነ ዘበሰማያት ይዘዝ (ይናዝዝ)

ስብሐት ለእግዚአብሔር፤
ወለወላዲቱ ድንግል፤
ወለመስቀሉ ክቡር። አሜን

# የአእላፋት

# መዝሙር

+ በስመ አብ ወወልድ +
ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ
አምላክ አሜን

# ይኸው (እሰይ) ተወለደ

ይኸው ተወለደ የዓለም መድኃኒት /3/
እሰይ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/
አዝ
ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ ሁሉ (3)
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ (3)
አዝ
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ /3/
የእስራኤል ንጉሥ ተወልዷል እያሉ /3/
አዝ
ሰብአ ሰገል መጡ እጅ መንሻ ይዘው /3/
ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤውን ገበሩለት ሰግደው /3/
አዝ
ምእመናን እንሂድ ከልደቱ ቤት/3/
ውኃው ሆኗልና ማርና ወተት/3/
አዝ
በሶርያ ታየ ፈጣሪ እንደ እንግዳ/3/
ብሥራት ልደቱን ለሁሉ ሊያስረዳ/3/

# ሰብሕዎ ለአምላክነ

ሰብሕዎ ለአምላክነ ሃሌ ሉያ ለእግዚአብሔር /2/

በሰማይ በምድር /6/

አዝ

ሰማዩን ያለ ምሰሶ አጽንቷል በቃሉ

መሬትን በውኆች መሐል መሥርቷል ድንበሩን

ይታያል ያበራል ጌታ ዛሬም በሥራው

ምስጉን ነው ሠራዊት ኹሉ ያመሰገነው

አዝ

ምሕረቱ ይቅርታው ብዙ ከወሰን የሰፋ

አባት ነው ብርቱ መጠጊያ የሰው ልጆች ተስፋ

መጋቢ ለፍጥረተ ዓለም ታላቅ ባለ ጸጋ

ያብባል ይለመልማል እርሱን የተጠጋ

አዝ

ተመስገን ተመስገን ይላል የተጎበኘ ሰው

ከጥፋት ከጉስቁልና ከሞት የመለሰው

ይቀባል ከታች አንሥቶ ከእረኝነት ቦታ

ይቅርታው ጸጋው ብዙ ነው ምሕረቱ የጌታ

አዝ

መላእክት በላይ በሰማይ ይዘምሩለታል

ዳዊትም ከበገናው ጋር ለቅኔ ተነሥቷል

በምድርም እኛ ልጆቹ እንበል ንሴብሖ

ይገባል ለአምላከ እስራኤል ውዳሴ አንክሮ

# በብርሃኑ ተመላለሱ

ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ/2/

ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ

የፍቅርን ሕይወት እንድትለብሱ

ኑ በብርሃኑ ተመላለሱ

አዝ

ሁሉን በሚችል በአምላክ ጥላ

በእረፍት ውኃ ስር አርፈናልና

ሰላምና ፍቅር ሕይወት በሚሰጥ

ወደ ጌታችን እንሂድ እንሩጥ

አዝ

ምሕረትና ፍርድ በእጁ የያዘው

የሰላም አባት መድኃኔዓለም ነው

ሕይወት የሆነን በመስቀል ውሎ

ብርሃንን ሰጠን ጨለማን ሽሮ

አዝ

የሚያስደነግጥ የሚያስጨንቀን

ይጠፋልና እርሱን ተማጽነን

በቀን ከሚበር ፍላጻ ሁሉ

ይታደገናል በቅዱስ ቃሉ

አዝ

እግርህ በድንጋይ እንዳይመታ

በፈተና ውስጥ እንድትበረታ

መቅሠፍት ከቤትህ እንዲከለከል

ይጠብቅሃል ሌሊትና ቀን

አዝ

ስሙን ያወቀ ሕይወት መሆኑን

ይመላለሳል ከኃይል ወደ ኃይል

ረጅም ዕድሜ ይጠግባል እርሱ

ብርሃን ይሆናል የጸጋ ልብሱ

አዝ

አቤቱ አንተ ተስፋ ነህና

የምትመግብ የፍቅር መና ማዳንህ

እኛን አስደስቶናል

እንዲህ ያለ ክብር ከየት ይገኛል

# አይኖቼ ማዳኑን አይተዋልና

አይኖቼ ማዳኑን አይተዋልና /2/ ይገባዋል /2/ ክብርና ምስጋና

ከሰማይ ወረደ ሰውን በማፍቀር ኃያሉ ጌታችን ቸሩ እግዚአብሔር

በቤተልሔም ዋሻ በዚያ በግርግም ተወለደ ዛሬ መድኃኔዓለም

አዝ

የተነበዩለት ብዙ ነቢያት ከድንግል ተወልዶ አዳነን በእውነት

ከበደል ጉራንጉር አነሣን ከትቢያ በአንድነት እንዘምር እንበል ሃሌሉያ

አዝ

የተናቅን ስንሆን እኛን ሊያከብር ወድዶ በፍቅር አከበረን ራሱን አዋርዶ

ምን ዓይነት ፍቅር ነው ፍጹም ምሕረት የአምላክ መወለድ በከብቶች በረት

አዝ

በንጽሕና ጸንተሽ ቤተ መቅደስ የኖርሽ በሕቱም ድንግልና መድኃኒትን ወለድሽ

የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ ጌታ ተወልዷል ከድንግል የሰዎች አለኝታ

# የጥበብ ሰዎች መጡ

ሰማይና ምድር የማይወስኑት (2)

ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት (2)

ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ (2)

አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ (2)

የጥበብ ሰዎች መጡ/2/ሰምተውት በዜና

እያበራላቸው ኮከቡ እንደፋና /2/

ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ (2)

ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ (2)

ከአንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን (2)

ኵነኔን አጥፍቶ ክብሩን ሊያወርሰን (2)

አዝ

ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም (2)

ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም (2)

እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት (2)

ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት (2)

አዝ

ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ (2)

የእስራኤል ንጉሥ ወዴት ነው እያሉ (2)

እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ (2)

ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ (2)

# ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ(፪) ለኖኅ ሐመሩ

“ ለአሮን በትሩ

“ ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ

“ የጌዴዎን ጸምሩ

“ ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ

“ ለፍሬ ስብሐት መፆሩ

እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ (2)

ሰላም ለኪ ሠረገላሁ ለአሚናዳብ

“ መና ያለባት ንጹሕ መሶብ

“ ያዕቆብ ያያት በሎዛ

“ የይስሐቅ መዓዛ

እንዘ ንሴፈዎለበረከትኪ ዘምስለ አምኃ ንሰግድ ለኪ (2)

ሰላም ለኪ ኅብስተ መና ዘእሥራኤል

“ ለአሮን በትሩ

“ ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ

“ የጌዴዎን ጸምሩ

“ ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ

“ ለፍሬ ስብሐት መፆሩ

እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ (2)

# ሃሌ ሃሌሉያ

ሃሌ ሃሌ ሉያ (2x)

በሰማይ በምድር ምሕረት ሆኗልና

ሃሌ ሃሌ ሉያ አሜን ሃሌ ሉያ

መላእክት ዘመሩ አመሰገኑት

እየተደነቁ በአምላክ ቸርነት /2/

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት አሉ

እረኞችም አብረው እርሱን አከበሩ /2/

አዝ

ዓለምን ለመፍጠር ከተጠበበበት

ይበልጣል ከሁሉ እኛን ያዳነበት (2)

ከዳግማዊት ሔዋን ከእመቤታችን

በረቂቅ ጥበቡ ተወልዶ አዳነን

አዝ

ሁላችሁም ሂዱ ከቤተልሔም

ታገኙታላችሁ በከብቶች ግርግም (2)

ኢየሱስ ክርስቶስ ወህቤ ሰላም

ሞታችንን ወስዶ ሕይወቱን ሰጠን (2)

# ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው

ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው
በመጠቅለያም ጠቀለለችው
የለምና ስፍራ በእንግዶች ማረፊያ
ግርግም አስተኛችው በከብቶች
ማደሪያ(x2)
[አዝ…]
ጨነቃት ጠበባት የዳዊት ከተማ
የጌታ መወለድ ተአምሩ ሲሰማ
ወረደ መልአኩ ምሥራች ሊያወራ
የሕፃኑም ክብር በምድር አበራ
ይህ ምሥጢር ግሩም ነው ከቶ 'ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር (x2)
[አዝ…]
ሰብአ ሰገል መጡ ከሩቅ ምሥራቅ ሀገር
ወርቅ ዕጣን ከርቤውን ለእርሱ ለመገበር
በእናቱም እቅፍ አገኙት ሕፃኑን
ለዓለም ተናገሩ ንጉሥ መወለዱን
ይህ ምሥጢር ግሩም ነው ከቶ 'ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር (x2)
[አዝ…]
የይሁዳ ምድር ምስጋናን ተመላ
ንጉሥ መጥቷልና ከናዝሬት ገሊላ ተአምሩን ትናገር
ቤተልሔም ታውራ ዝማሬ ሲውጣት ተረስቶ ቆጠራ
ይህ ምሥጢር ግሩም ነው ከቶ 'ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር (x2)
[አዝ…]
የማይታይ ታየ ተዳሰሰ እንደ ሰው
በጠባቡ ደረት አዳምን መሰለው ገረማት ጥበቡ
ታናሿን ሙሽራ ተዋሕዷልና ቃል ከሥጋ ጋራ
ይህ ምሥጢር ግሩም ነው ከቶ 'ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር (x2)

# የመላእክት አለቃ

የመላእክት አለቃ ገብርኤልን ላከው
ኃያሉ እግዚአብሔር በሰማያት ያለው
የባሕርይ ልጁ ወደ አንቺ ይመጣል
ብለህ ለጽዮን ልጅ ንገራት ለድንግል
አዝ
ኃይለ ልዑል ወልድም ሥጋሽን ይለብሳል
በተለየ አካሉ ወደ አንቺ ይመጣል
ከሥጋሽም ሥጋ ከነፍስሽም ነፍስ ነሥቶ ይዋሐዳል
በግዕዘ ሕፃናት ከአንቺ ይወለዳል
አዝ
ደንቆሮ ሊሰማ ድዶች ሊናገሩ
በጌታ ተአምራት ዕውራን ሊበሩ ሙታን
ይነሡ ዘንድ በማሕፀንሽ ፍሬ
ከእግዚአብሔር ወደ አንቺ ተልኬአለሁ ዛሬ

አዝ
ደስ አሰኛት አለው በልዩ ሰላምታ ሐሴት
እንድታደርግ ምሥራቹን ሰምታ ድዳ
እንዳደረግከው ካህን ዘካርያስን
እንዳታሳዝናት ከእርሷ ጋር ስትደርስ
አዝ
ገብርኤል በደስታ ምሥራቹን ይዞ
ከሰማይ ወረደ በአምላኩ ታዝዞ
በሊባኖስ መንደር እስኪሰማ ድረስ
ክንፉን እያማታ መጣ ሲገሰግስ
አዝ
ደስ ይበልሽ አላት እየተሳለማት ሐርን
ከወርቅ ጋር ስትፈትል አግኝቷት
እውነተኛው ንጉሥ ከአንቺ ይወለዳል
ለአንቺ ፍቅርና አንድነት ይገባል

# ሰላም ለኪ እያለ

ሰላም እለኪ እያለ (2)
ሐርና ወርቁን ስታስማማ
የገብርኤል ድምፅ ተሰማ
ተሰማ የመልአኩ ድምፅ
ተሰማ ተሰማ የገብርኤል ድምጽ ተሰማ
አዝ
ውሃ ስትቀጂ ክንፉን እያማታ
ሊያበስርሽ የመጣው በታላቅ ደስታ
ከሞገስሽ ብዛት (2) ሲታጠቅ ሲፈታ
አቅርቦልሽ ነበር የክብር ሰላምታ
አዝ
የምሥራቹን ቃል ምስጢር ተሸክሞ
ገብርኤል ተላከ ሊያረጋጋት ደግሞ
እርጋታ ተሞልታ (2) ነገሩን መርምራ
የመልአኩን ብሥራት ሰማችው በተራ
አዝ
ይደሰታል እንጂ መንፈሴ በአምላኬ
በምስጋና ሳድር ዘወትር ተንበርክኬ
ሃሳቤ ለቅፅበት (2) ሌላ መቸ ያስባል
ለእኔ ልጅን መውለድ እንዴት ይቻለኛል
አዝ
ከአንቺ የሚወለደው ልዑል ነው ክቡር
የተመሰገነ በሰማይ በምድር
ምስጢሩ ኃያል ነው (2) ይረቃል ይሰፋል
ከአንቺ በቀር ይኼን ማን ይሸከመዋል
አዝ
እጹብ ነው ድንቅ ነው አንቺን የፈጠረ
አንቺን በመውደዱ ሰውን አከበረ
ዓለም ይባረካል (2) በማሕፀንሽ ፍሬ
ክብርሽን አልዘልቅም ዘርዝሬ ዘርዝሬ

# በኤፍራታ ምድር

በኤፍራታ ምድር በቤተልሄም/2/

ጌታ ተወለደ ከድንግል ማርያም/2/

ብርሃናዊው ኮከብ ከሰማይ ዝቅ አለ/2/

ፍጥረትም ዘመረ ሃሌ ሉያ እያለ/2/

አዝ............

መንጋውን በሌሊት ሲጠብቁ እረኞች

ከሰማይም ሰሙ ታላቅ የምሥራች

በመላእክቱ ግርማ ምድር ስታበራ

የሚያስጨንቅ ነበር እጅግ የሚያስፈራ

አዝ..........

ድንገትም የሰማይ ሠራዊት ተገልጠው

በአንድነት ዘመሩ ከኖሎት ጋር ሆነው

ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም

ብለው ሰላምን በምድር በጎ ፈቃድ

ለሰው

አዝ..........

ቤተልሔም ሄደው ጌታን ተሳለሙት

ከእናቱ ጋር ሆኖ በግርግም አገኙት

የመላእክትን ዜና እረኞች አወሩ

በልዩ ምስጋና አምላክን ሲያከብሩ

አዝ.........

ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ፍሥሓ ደስታ

በዳዊት ከተማ ተወለደ ጌታ

ሕፃን ከእናቱ ጋር በግርግም ፈለጉት

እርሱ ነው ለሰዎች የድኅነት ምልክት

# በጎል ሰከበ

በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ/2/

ቤዛ ኵሉ ዓለም/2/ ዮም ተወልደ/2/

ቤዛ ኩሉ

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ/2/

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ/2/

# ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት

ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት (2)

ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሉያ (3) አሜን ሃሌ ሉያ

# ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን /4/
እንደ መላእክቱ ብርሃንን ለብሰን
ገና እንዘምራለን
------
ወላዲተ አምላክን ከፊት አስቀድመን
በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን
ለሥላሴ ክብር ገና እንዘምራለን
ገና እንዘምራለን
አዝ
በምስጋና ሥራ ከሠለጠኑት ጋር
ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን
ያልተሰማ ዜማ ያልታየ ምስጋና
ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቡና
ገና እንዘምራለን
አዝ
በትዕቢትም ሳይሆን በታላቅ ትሕትና
በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቡና
ሥራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና
ገና እንዘምራለን
አዝ
ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም
ሜልኮል በዝማሬው ብትስቅበትም
አምላክ ከወደደው እንዲያመሰግነው
በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ማን ነው
ገና እንዘምራለን

# ዝም አትበሉ

ዝም አትበሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ (2)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ቅዱስ በሉ
መላእክትን ሁኑ ምስጋናን ጀምሩ
ሥሉስ ቅዱስ በሉ
--------
የሙሴ እኅት ማርያም ከበሮውን አንሺው
በምስጋና መዝሙር እስራኤልን ጥሪው
አምላክን እናክብር እንዘምር በእልልታ
ከእኛ ጋር ይሆናል የሠራዊት ጌታ (2)
አዝ
ፍጥረታትም ጩኹ ሰማያት ዘምሩ
ስለ ቅድስናው ውዳሴን ጀምሩ
ዳዊት ሆይ ተነሣ ስለ ጽዮን ዘምር
ከበሮው ይመታ በገናው ይደርደር (2)
አዝ
ወገኖች እንዘምር ለእግዚአብሔር ክብር
ውለታው ብዙ ነው ለእኛ ያለው ፍቅር
ማዳኑን ያያችሁ ዘምሩ በዕልልታ
ለጌታ ለእግዚአብሔር ለሠራዊት ጌታ (2)
አዝ
ባሕሩን አቋርጦ ወንዝ ያሻገራችሁ
ተራራውን ንዶ ያቀለለላችሁ
በዓውሎ ነፋስ መሐል መንገድ ላለው ጌታ
ለንጉሥ ክርስቶስ እንዘምር በዕልልታ (2)

# ወዳንቺ የመጣው

ወዳንቺ የመጣው በብሩህ ደመና

ከሦስቱ አካል አንዱ ክርስቶስ ነውና

የጠፋ በግ አዳም ታደሰ በጌታ

ባንቺ ተፈጸመ የሰው ልጆች ደስታ

አዝ

በደይን የተጣለች ሔዋን ተደሰተች

የደስታ መፍለቂያ አንቺን ስላገኘች

የበረከት ፍሬ ከአንቺ ተገኘልን

የወይን ቦታ ነሽ ድንግል እናታችን

አዝ

ወልድም ባሕርይሽን ባህሪ አድርጎት

ለፍጥረታት ጌታ መአዛሽ ተስማምቶት

ከአንቺ ይወለድ ዘንድ ፍጹም ሊላላክሽ
በጥቂት አደገ ተልኮና ታዞሽ

አዝ

ከድንግልና ጋር አንድ የሆነ ሀሊብ

በሩካቤ ሳይሆን በብስራት እንደ ንብ

ከሆድ መጥበብ ጋር የመለኮት ስፋት

አንቺ ሆነሽ ሳለ ታናሿ ሙሽሪት

አዝ

በፍጡር ህሊና የማይመረመር

እጹብ ነው ድንቅ ነው የመጽነሷ ነገር

እሳተ ነበልባል በሆድሽ ውስጥ ሲያድር

ነደ ነበልባሉ አልፈጀሽም ነበር

# አንቺ አንቺ ቤተልሔም

አንቺ አንቺ ቤተልሔም የይሁዳ መሬት
በአንቺ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
አዝ

ለአዳም ክብር ሲሻ ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም
ጌታ ተወለደ ቤተልሔም
ከድንግል ማርያም ቤተልሔም
አዝ
እጅ መንሻ አቀረቡ ቤተልሔም
የምሥራቅ ነገሥታት ቤተልሔም
በከብቶቹ በረት ቤተልሔም
ተኝቶ ላገኙት ቤተልሔም

አዝ
እስራኤል ሕዝቤን ቤተልሔም
የሚጠብቃቸው ቤተልሔም
ከአንቺ ይወጣል ብሎ ቤተልሔም
እንደነገራቸው ቤተልሔም
አዝ
ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም
ያሸበሸቡልሽ ቤተልሔም
ስብሐት ለእግዚአብሔር ቤተልሔም
ብለው ዘመሩልሽ ቤተልሔም
አዝ
አንቺ ቤተልሔም ቤተልሔም
እንዴት ታድለሻል ቤተልሔም
ኢዮር እና ራማ ቤተልሔም
ኤረርን መስለሻል ቤተልሔም

# የምሥራች ደስ ይበለን

የምሥራች ደስ ይበለን (2)

የዓለም መድኃኒት ተወለደልን (2)

ምሥራች ደስ ይበለን

-------------

አዝ

ኢየሱስ የዓለም ቤዛ (2)

የዓለም ቤዛ /3/ ለእኛ ተወለደልን

አዝ

ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ሲሰማ (2)

ፈልጋችሁ አምጡት በቀን በጨለማ (2)

አዝ

ሰብአ ሰገል እንደታዘዙት (2)

በኮከብ ተመርተው ሕፃኑን አገኙት (2)

አዝ

ሰገዱለት ከመሬት ወድቀው (2)

ወርቅና ዕጣኑን ከርቤውንም ሰጥተው (2)

# እሰይ እሰይ ተወለደ

እሰይ እሰይ ተወለደ
እሰይ እሰይ ተወለደ
ከሰማየ ሰማያት ወረደ
ከድንግል ማርያም ተወለደ
---------
እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
ቸሩ አባታችን እሰይ እሰይ
እርሱ ባይወለድ እሰይ እሰይ
መድኃኒታችን እሰይ እሰይ
መቼ ትገኝ ነበረ እሰይ እሰይ
ገነት ምድራችን እሰይ እሰይ
አዝ
ብርሃን ወጣላቸው እሰይ እሰይ
ለእውነት ወገኖቹ እሰይ እሰይ

በጨለማው መንገድ እሰይ እሰይ
እንዳይሰላቹ እሰይ እሰይ
አዝ
እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ
አንድያ ልጁን እሰይ እሰይ
እርሱ ወዷልና እሰይ እሰይ
እንዲሁ ዓለሙን እሰይ እሰይ
አዝ
እንደ ጠል ወረደ እሰይ እሰይ
ከሰማይ ወደ እኛ እሰይ እሰይ
ወገኖቹን ሊያድን እሰይ እሰይ
ከሰይጣን ቁራኛ እሰይ እሰይ

# ማርያም ተዐቢ

ማርያም ተዐቢ እምኵሉ ፍጥረት

ኢያውዓያ እሳተ መለኮት

# እም ሰማያት ወረደ

እም ሰማያት ወረደ ወእም ማርያም ‘ተወልደ’(2)

ከመ ይኩን ቤዛ (2) ለኩሉ ዓለም ለብሰ ሥጋ ማርያም (2)

# ዮም ሰማያዊ

ዮም ሰማያዊ በኀል ሰከበ ለዘተወልደ እም ቅድስት ድንግል (2)

ርእይዎ ኖሎት/2/ አእኰትዎ መላእክት/2/

# ተወልደ ኢየሱስ

ተወልደ ኢየሱስ <u>በቤተልሔም</u> (2)

ዘይሁዳ በቤተልሔም (2)

አዋልደ ጢሮስ ‘<u>አሜሃ ይሰግዳ’</u> (2) በቤተልሔም (2)

# አንፈርዓጹ

አንፈርዓጹ ሰብአ ሰገል (2)

አምኃሆሙ አምጽኡ መድምመ (2)

# ድንግል በድንግልና

ድንግል በድንግልና ፀንሳ
በድንግልና ትወልዳለች
ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች
አዝ
ገና ሳይፀነስ ዘመኑ ሳይገባ
ገረድ መሆን ሻተች ትንቢቱን አንብባ
ልታያት ናፈቀች ያቺን ቅድስት እናት
ለክብርዋ ተገዝታ ውኃ ልትቀዳለት
አዝ
ባርያ ልሁን አለች ዝቅ አድርጋ ራሷን
መች አወቀችና እናቱ መሆኗን
ጥቂት ለሚሻ ሰው ያውቃል ብዙ መስጠት
በማሕፀኗ መቅደስ ሲቀደስ ኖረበት
አዝ
ሐር ወርቁን ስትፈትል በቤተ መቅደሱ
ማደርያው እንድትሆን መረጣት ንጉሡ
በሕሊናው ተስላ የነበረች ምናብ
መሰላል ሆነችው ለአዳም ድኅነት እርከብ
አዝ
በጎ መዓዛዋን ውበቷን ወደደ
በማሕፀኗ ሊያድር እግዚአብሔር ወረደ
ከኪሩቤል ይልቅ ጀርባዋ ተመቸው
ንጽሕት ናትና የማትቆረቁረው

# ድንግል በድንግልና

አዝ

የተዘጋች መቅደስ ከቶ 'ማትከፈት

ታትማ የኖረች የክብሩ ሰገነት

ማንም አይከፍታትም ጥበብ አላትና

የእስራኤል ቅዱስ ገብቶባታልና

አዝ

በረቀቀው ጥበብ ድንግል ተደነቀች

በሆዷ ቅዳሴን እያስተናገደች

ጎንበስ አለች ማርያም ውዳሴ ልትሰማ

ከቅኔያት ሀገር ከሆዷ ከተማ

# አብሠራ ገብርኤል

አብሠራ ገብርኤል ለማርያም (2x)

ወይቤላ (x2) ትወልዲ ወልደ

ሚካኤል መልአክ በክነፍ ጾራ

መንጦላዕተ ደመና ሰወራ

ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙስና

ተወልደ ወልድ እምኔሃ

ገብርኤል ማርያምን /አበሠራት/ (x2)

ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ አላት

ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት

የሰማይ መጋረጃውም ሸፈናት

ንጽሕት ናትና በድንግልና (x 2)

ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና

አዝ /ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት/

አዳም በጥፋቱ ከገነት ሲባረር

በሚካኤል ክንፎች ቀድሞ አይቶሽ ነበር

ሔዋንን ሲጠራት ሕይወቴ ነሽ አላት

እንደሚድን አውቆ ድንግል በአንቺ ምክንያት

ንጽሕት ናትና በድንግልና

ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና

አዝ /ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት/

እግዚአብሔር የላከው የከበረው መልአክ

ድንግል ሆይ ለክብርሽ አየን ሲንበረከክ

በፍቅር በትሕትና በፍጹም ሰላምታ

የጌታን ሰው መሆን ነገረሽ በደስታ

ንጽሕት ናትና በድንግልና

ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና

# አብሠራ ገብርኤል

አዝ /ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት/
ደስተኛይቷ ሆይ ደስ ይበልሽ ድንግል
የአብ ቃል ክርስቶስ ሥጋሽን ይለብሳል
አንቺም ትይዋለሽ ስሙን ኢየሱስ
መድኃኒት ነውና ለሥጋ ወነፍስ

ንጽሕት ናትና በድንግልና
ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና
አዝ /ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት/
እንደ ኒቆዲሞስ ሳትከራከሪ
እንደ ዘካርያስ ሳትጠራጠሪ
ይኩነኒ ብለሽ ቃልን ተቀብለሽ
ከፍጥረቱ ማነው አንቺን የሚመስልሽ
ንጽሕት ናትና በድንግልና
ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና

አብሠራ ገብርኤል ለማርያም ወይቤላ (x2)
ትወልዲ ወልደ ሚካኤል መልአክ በክነፍ ጾራ
መንጦላዕተ ደመና ሰወራ
ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙስና
ተወልደ ወልድ እምኔሃ
ገብርኤል ማርያምን /አበሠራት/ (x2)
ወንድ ልጅን ትወልጃለሽ አላት
ሚካኤል መልአክ በክንፉ ከለላት
የሰማይ መጋረጃውም ሸፈናት
ንጽሕት ናትና በድንግልና (x 2)
ጥፋት የለባትምና ወንድ ልጅን ወልዳልናለችና

# ስምህ በሁሉ ተመስገነ

ስምህ በሁሉ ተመስገነ

ከክብር በላይ ክብርህ ገነነ

አንተን ማወደስ ያስደስተናል

ስምህን ማክበር ግብራችን ሆኗል

-----

አምላክ ተመስገን በሰማያት

ስምህ ይወደስ በፍጥረታት

ከሕፃናት አፍ ምስጋና ይውጣ /2/

አንተን ማመስገን ይሁን የእኛ ዕጣ /2/

አዝ

በምግብ እጦት ብንሰቃይም

ማኅሌትህን አናቋርጥም

የመከራ ዶፍ ቢወርድብንም /2/

እንዘምራለን ለአምላካችን ስም /2/

አዝ

ሰማዩ ዝናብ ደመና ቢያጣም

ፍቅርህ በእኛ ውስጥ አላቋረጠም

ቸርነትህን እንጠብቃለን /2/

ከአንተ ደጅ አምላክ/ጌታ/ የት እንሄዳለን /2/

# ተወለደ ጌታ ተወለደ

ተወለደ ጌታ ተወለደ
ተወለደ አምላክ ተወለደ
ተወለደ ጌታ ተወለደ
ተወለደ አምላክ ተወለደ
-------------------------
አንዲት ብላቴና የዓሥራ አምስት ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላእክት አዋጅ
በኅቱም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የሚያድን የሰዎች አለኝታ
አዝ..................................
ይህ ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት
እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋሕዶ
አየነው አምላክን እንደሰው ተወልዶ

አዝ..................................
ፍጹም ድንግልና ክብር የተመላች
እንደምን አምላክን በማሕፀን ያዘች
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ ወለደችው
ድንግል የሔዋን አለኝታ
አዝ.......................................
አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም
በምድር ተፈልጎ እንደ አንቺ አልተገኘም
በአሳብ በግብር ንጹሕ ስለሆነች
የአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

# መድኃኒነ ተወልደ ነዋ

መድኃኒነ ተወልደ ነዋ /2/

ይእዜኒ ለሰላም ንትልዋ/4/

# አማን በአማን

አማን በአማን /2/ መንክር

መንክር ስብሐተ ልደቱ /2/